የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
Ethiopian Environmental Protection Authority

2016

በሲዳማ ክልል ወንሾ ወረዳ



በአገር በቀል ዕውቀት
የተፈጥሮ ደንና አካባቢ ጥበቃ
ላይ የተሰራ ተሞክሮ

epa.gov.et

ሚያዝያ/2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

መግቢያ .....

1 ክፍል አንድ 1

1.1 ዓላማ 1

1.1.1 ዋና ዓላማ 1

1.1.2 ዝርዝር ዓላማዎች 1

1.2 አስፈላጊነት 1

1.3 ወሰን /ዳራ/ 1

1.4 መረጃውን ያሰባሰበው ቡድን 1

1.5 የመረጃ አሰባሰቡ ስልት 1

1.6 የሚጠበቁ ውጤቶች፡- 2

2 ክፍል ሁለት 2

2.1 ወንሾ 2

2.1.1 የአቦ ወንሾ ቦታ ሁኔታ 3

2.2 ባህላዊ አስተዳደር (አምልኮ) 5

2.3 የሹመት ሁኔታና አሰጣጥ ስርአት 6

2.4 የዳኝነት አሰጣጥ ስርአት 8

2.5 በአቦ ወንሾ ክልል ላይ የሚገኘው ደን ሁኔታ 8

2.6 የአቦ ወንሾ ስርአት በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያበረከተው አስተዋጽኦ 11

3 ያጋጠሙ ችግሮች 13

መግቢያ

ጤናማና ንፁህ አካባቢ መኖር የዜጎች መሰረታዊ መብት ነው ። ይህንኑ ለማረጋገጥ ደግሞ አካባቢን አረንጓዴ ፣ፅዱ እና ለጤና ምቹ ማድረግ እንዲሁም የአካባቢ መጎዳትን እና መራቆትን በመቀነስ የተሻለ አካባቢን ማቆየት አስፈላጊ ነው ።

በተለያዩ ቦታዎች ለተፈጥሮ ሀብቶች እንክብካቤ ካለመደረጉ የተነሳ ለተለያዩ ችግሮች የሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች በርካታ ናቸው። ከችግሩ ለመዳን ለአካባቢ መጎሳቆል ምክንያት የሆኑ ነገሮችን በመለየትና መፍትሄ መሻትና መተግበር ያስፈልጋል። በመሆኑም ሁሉም ተቋማት እንዲሁም ሁሉም ሕብረተሰብ በሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ የአካባቢን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ አካባቢውን ማልማት፣ ለጤና ምቹ ማድረግ እንዲሁም በውጤቱ መጠቀም ተገቢ ነው።

አካባቢ በአግባቡ በተያዘ ቁጥር ምቹ የአካባቢ ሁኔታና ጥሩ የአየር ንብረት ኖሮ ሕብረተሰቡ ንፁህ አየር እያገኘ በጤንነት የመኖር እድሉ ከፍ ይላል።አካባቢያችን ፅዱና ለጤና ተስማሚ እንዲሆን እና ዘላቂ የሀብት አጠቃቀም እንዲፈጠር የሚያደርጉ ዘዴዎች በርካታ ቢሆኑም አንዱና ዋነኛው ነባር የሆኑ በባህላዊ መንገድ እየተሠሩ ያሉ የሀገር በቀል ዕውቀቶች ናቸው። በመሆኑም አንዱጋ የተሰራውን መልካም ስራ በደንብ በማየትና መረጃውን በስፋት በማደራጀት እንዲሁም አሰራሩን በመተንተን ሌሎችም ቦታዎች ስልቱን ተጠቅመው እንዲሰሩ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

በሲዳማ ክልል በማዕከላዊ ዞን ወንሾ ወረዳ የባህላዊ አስተዳደርን በመጠቀም የተፈጥሮ ደንን የማቆየት እና አካባቢ እንዳይጎዳ የማድረግ ስራ በመስራት ለጤና ምቹ የሆነ አካባቢና የአየር ንብረትን መጠበቅ ችለዋል።

በመሆኑም በወንሾ ወረዳ ውስጥ "አቦ ወንሾ" በሚባል ቦታ የባህላዊ አስተዳደርን በመጠቀም የተፈጥሮ ደንና አካባቢ ጥበቃ ስራ ለመልካም ተሞክሮ የሚሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ይህ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

ክፍል አንድ

1.1 ዓላማ

1.1.1 ዋና ዓላማ

ሀገር በቀል ዕውቀትን በመጠቀም አካባቢን የመጠበቅ የማዳን ስራን የሚያሳይ መልካም ተሞክሮን በመለየትና በመቀመር ወደ ሌሎቹ እንዲስፋፋ ማድረግ ፤

1.1.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- ጠቃሚ የሆኑ ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ማበረታታትና ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ
- በተለያየ ቦታ ያሉትን ሀገር በቀል ዕውቀቶች ለሌሎች በአስተማሪነት እንዲስፋፉ ማድረግ

1.2 አስፈላጊነት

የተሻሉ የሀገር በቀል ዕውቀት አስተማሪ ስራዎችን በማየትና በተሞክሮነት ቀምሮ ሌሎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ከመስሪያ ቤታችን ዕቅድ ውስጥ አንዱ ነው። በተጨማሪም ግንዛቤ ከምናስፋፋበት ዘዴ ውስጥ አንዱ ጥሩ ልምድን በተሞክሮ በማለዋወጥ አንዱ ከሌላው እንዲማርና እንዲጠቀምበት ማድረግ ስለሆነ የሰሩትን ለማበረታታትና ለማነቃቃት ከመቻልም አልፎ ልምዱን ሌሎች እንዲማሩበት ለማድረግ ይህ የግንዛቤ ማስፋፊያ የሆነውን የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ስራ መስራት አስፈላጊ ነው።

1.3 ወሰን /ዳራ/፡-

የሀገር በቀል ዕውቀት የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ሥራው የተከናወነው በሲዳማ ክልል በማዕከላዊ ዞን ወንሾ ወረዳ ውስጥ "አቦ ወንሾ" በተባለ ቦታ ነው።

1.4 መረጃውን ያሰባሰበው ቡድን

የቡድኑ አባላት የአካባቢ መብቶች ግንዛቤ ማጎልበቻ ዲስክ ባለሙያዎች ሲሆኑ ወንድ 2 ሴት1 ወንድ 3 ናቸው።በተጨማሪም ዝርዝር ሁኔታን በማስረዳት ለመረጃ ማሰባሰቡ ሊያግዙ የሚችሉ ከወረዳው የተመደቡ 2 ወንድ ባለሙያዎችም ተሳትፈዋል፡

1.5 የመረጃ አሰባሰቡ ስልት

የአካባቢ መብቶች ግንዛቤ ማጎልበቻ ዲስክ ባለሙያዎች ከዲስክ ኃላፊ ጋር በመሆን ተሞክሮን ለማሰባሰብ የሚረዳ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት አስቀድሞ የክልልና የወረዳው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ዓላማውንና አስፈላጊነቱን እንዲያውቁት በማድረግ ነው።

በመቀጠልም የባለሙያዎች ቡድን በሥራው ላይ እንደተሠማራ በቅድሚያ ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲሁም ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ስለ ተልዕኮው ዝርዝር ሁኔታ በመወያየት በሀገር በቀል ዕውቀት አሰራር ተሞክሮ ተብሎ በተመረጠው አቦ ወንሾ በሚባል ቦታ በመገኘት የተለያየ ስልት በመጠቀም ማለትም ለተጠቃሚዎችና ለአካባቢ ሽማግሌዎች ቃለ-መጠይቅ በማድረግ፣ በአካል ቦታውን በመጎብኘት እና በፎቶ መረጃዎችን በመውሰድ መረጃ ተሰብስቧል።



ፎቶ 1 ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መረጃ ሲሰባሰብ

1.6 የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የተቀመረው መልካም ተሞክሮ ለሌሎች በአስተማሪነት ቀርቦ እንደራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ይጠቀሙበታል
- የመስክ ምልከታ የተደረገባቸው አካባቢ ያሉ ሠራተኞችና ሕብረተሰቡ ለተግባሩ ያላቸው ተነሳሽነት ይጨምራል።
- ጠቃሚ የሆነ የሀገር በቀል ዕውቀት አስፈላጊነት ትኩረት ያገኛል
- ሀገር በቀል ዕውቀትን ያስፋፋል


ክፍል ሁለት


2.1 ወንሾ

ወንሾ ወረዳ በሲዳማ ክልል በማዕከላዊ ዞን የምትገኝ ስትሆን ወንሾ ማለት በሲዳመኛ "ልሙላ ?" ማለት ነው። ወንሾ የሚለው የወረዳው ስያሜ የተወሰደው በወረዳው ውስጥ ካለው በባህላዊ እምነት ታዋቂ ከሆነው አቦ ወንሾ ከሚባለው ቦታ ስም ነው። የወንሾ ወረዳ ዋና ከተማ ቦካሶ የምትባል ሲሆን ወረደዋ 17 ቀበሌዎች እና 2 የከተማ መዘጋጃ አሏት። ከአቦ ወንሾ ቦታ ጋር ከቅርበታቸው የተነሳ ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው 7 ቀበሌዎች ናቸው። የነዚህ 7ቱ ቀበሌዎች ሕዝብ ብዛት ወ 24027 ሴ 23380 ድ 47,407 ናቸው።

ወንሾ ወረዳ ክልሏ ውስጥ 17 ቦታ ጥብቅ ደኖች ያሏት ሲሆን በአጠቃላይ የሁሉም ድምር 250 ሄክታር የሚሆን በጥብቅ ደን የተሸፈነ ቦታ አላት።ከነዚህ 17ቱ ጥብቅ ደን ቦታዎች ውስጥ ሰፊውና

ታዋቂ እንዲሁም በተፈጥሮ ደን የተሸፈነው 92.34 ሄክታር የሆነው የአቦ ወንሾ የተፈጥሮ ደን ነው።





ፎቶ 2 ወንሾ ወረዳ ያሏት ደኖች

2.1.1 የአቦ ወንሾ ቦታ ሁኔታ

የአቦ ወንሾ ቦታ የሚገኘው በወንሾ ወረዳ ሲሆን ግማሹ በአጥር የተከለለ ሆኖ የአመራር ስርአቱ የሚከናወንበት ቦታ ሲሆን ቀሪው ቦታ ደግሞ ከአጥር ውጭ ሆኖ በደን የተሸፈነ ነው።

ቦታው በዋናነት 4 ነገሮች ይከናወኑበታል። እነሱም

1. ባህላዊ አምልኮ
2. ባህላዊ ዳኝነት
3. ባህላዊ የተፈጥሮ ደን ጥበቃ
4. የዱር አራዊት እንዳይታደኑ ክልከላ ተግባራት በዋናነት ይከናወንበታል።

እነዚህ ተግባራት ሲከናወኑ የቆዩበት ወቅት ወደ 18 ትውልድ አስቆጥረዋል በሚል በተለያዩ በቦታው በሚገኙ ሰዎች ተገልጸልናል። ቦታው ዙሪያውን በወንዝ የተከበበ ሲሆን አይሾ እና ናኒጋ የሚባሉት ወንዞች በዋናነት ይታወቃሉ።

ቦታው ያለበት ክልል ባለቤት የህዝብ(የወል) ቦታ ሲሆን እያስተዳደሩ ያሉት ለቦታው አስተዳዳሪነት የተሾሙት ናቸው። ግቢው በሁለት ዙር በእንጨት አጥር የተከበበ ሆኖ ፅዳቱ በስርአት የተጠበቀ ነው። በግቢው ውስጥ በተለያየ ቦታ የፌዴራል እና የክልሉን ሰንደቅ ዓላማ ቆመው ያውለበልባሉ። በግቢው ውስጥ በርካታ ቤቶች አሉ። ሁሉም ቤቶች በውስጣቸው ከሚከናወነው ተግባር አንፃር እያንዳንዳቸው ስያሜ አላቸው። ቤቶቹ ከጣራው ቆርቆሮ በስተቀር ቀሪዎቹ የተፈጥሮ ውጤቶች ሆነው ባህላዊ ነገሮች ይታይባቸዋል። ግድግዳና ጣራ የተሰራበት እንጨቱ፣ ግድግዳ የተመረገበት ጭቃው፣ ግድግዳ ላይ የተለጠፈው ከቀርቀሀ የተሰራው ሳጠራ፣ የእንጨት በርና መስኮት፣ ቤቱ ውስጥ ያሉት የእንጨት መቀመጫ፣ ለመኝታ አገልግሎት እየሰጠ ያለው የከብት ቆዳ(ቁርበት)፣ ፍትህ ሰጪው ሰው የሚቀመጥበት ከቀርቀሀ የተሰራ ዙፋን እና ሌሎቹም ያየናቸው ሀገር በቀል እና ባህላዊ ነገርን የሚያስታውሱ ናቸው።



ፎቶ 3 የአቦ ወንሾ አጥር ግቢ መግቢያ



ፎቶ 4 የአቦ ወንሾ ግቢ ገፅታ

2.2 ባህላዊ አስተዳደር (አምልኮ)

አቦ ወንሾ በባህላዊ መስተዳድር ስራ የባህላዊ አስተዳደር የሚከናወንበታ ቦታ ነው። ባህላዊ ፍትህ ፍለጋ ባለጉዳዮች ሲመጡ በመጀመሪያው ግቢ አረፍ ካሉ በኋላ ወደ ሁለተኛው አጥር ውስጥ ገብተው በሚመለከተው ቤት/ክፍል ውስጥ እንዲገቡ ተደርጎ የመጡበትን ጉዳይ ያቀርባሉ።

በቦታው ላይ የክርስቲያንም ሆነ የሙስሊምም እምነት ተከታይ ተጠሪዎች ይገኛሉ ። በዚሁ መሰረት የማንኛውም ሀይማኖት ተከታይ ቢመጣ በእኩል ይስተናገዳል። በግቢው ፍትህ አሰጣጥ እየተገለገሉ ያሉት ሲዳማዎች ብቻ ሳይሆኑ ከሌላም ቦታ በመምጣት አገልግሎት እያገኙ መሆኑን አስጎብኚአችን ገልፀውልናል። በዚህ ግቢ ውስጥ በሚከናወነው ተግባር አምነው የሚከተሉ ሰዎች ለአቦ ወንሾ ስለት እየተሳሉ ስለቱን ያቀርባሉ። ለስለት የመጣው በሬ/በግ ግቢ ከመግባቱ በፊት በዳንሺኞ ቅጠል ይታጠባል። እርድ የሚፈፀመው በክብ ቅርፅ የተሰራ ቤት ውስጥ በአቦ መቃብር ላይ ሲሆን እርድ በሚከናወንበት ቦታ/ቤት እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው ሰዎች ትላልቅ የተባሉ ሽማግሌዎች እና ለስራው ቅርበት ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። ከእርዱ በኋላ የሚገፈፈው ከቤት ውስጥ ወጥቶ ራቅ ባለ ቦታ በአጥር ውስጥ ነው። በዚህ መሰረት ቆሻሻውም በዛው በስርዓት ይወገዳል። "ግቢዬን ፣ ውሃዬን ከጠበቅህ ካፀዳህ እኔም አንተን ፣ ቤተሰብህን እጠብቃለሁ" ብሎ ህልም ስለሚያሳይ ሁሉም ያፀዳል። ለፅዳትም ትኩረት ይሰጣል።

ሁሉም ያነጋገርናቸው ሰዎች በገለጹልን መሰረት አምልኮው ከአምላካቸው ጋር የሚገናኝ ነው ብለው ያምናሉ።አምልኮውና ጸሎቱ ትኩረት የሚያደርግባቸው ጉዳዮች አሉ።ሀገር ደህና እንድትሆን፣ መሃን እንድትወልድ፣ የተቸገረ እንዲያገኝ፣ አዝዕርት እንዲለማ፣ የተትረፈረፈ ምርት እንዲገኝ፣ የእርስ በእርስ ፍቅር እና መተማመን እንዲኖር፣ መከዳዳት እንዳይፈጠር

ጸሎት በማድረግ አምልኮው ይከናወናል።ሽማግሌዎች በየም በጸሎት ይለምናሉ።ፀሎታቸውን በማድረግ የሚያመልኩት ለአቦ ነው።አቦ ደግሞ ከፈጣሪ ጋር ያገናኛል ያስታርቃል በሚል ይታመናል።



ፎቶ 4 ፡- የአምልኮቱ ቦታና ስለት አቀራረብ

2.3 ሹመት የአሰጣጥ ስርአት

አቦ የአካኮ ልጅ ናቸው፣ አካኮ የአሸማ ልጅ ናቸው(አሸማ አካኮን ወለዱ፣ አካኮ አቦን ወለዱ) በዚህ መሰረት ከአቦ ጀምሮ አሁን እስካለበት ድረስ 18 ትውልድ ደረሰ በሚል በቦታው ላይ ያሉት ሰዎች ገልፀውልናል። አሸማ፣ አካኮ እና አቦ የሦስቱም የክብር ስም ነው ሌላ መጠሪያ ስማቸው አይታወቅም። ሦስቱም ስማቸው በከንቱ አይነሳም ስማቸውን በከንቱ የሚያነሳ ቢኖር ይቀሰፋል ተብሎ ይታመናል።


አቦ ሁለት(2) ሚስት አገቡ እና ከአንደኛዋ የተወለዱት 9 ሲሆኑ ሆሎ ተባሉ። ከሁተኛዋ ሚስት የተወለዱት ደግሞ 5 ሲሆኑ ገርቢቾ ተባሉ። በዚህ መሰረት ከነዚህ ከሦስቱ የዘር ሀረግ በሲዳማ ውስጥ ሆሎ እና ገርቢቾ የሚባሉ ጎሳዎች ተፈጠሩ። ሆሎ 9 ጎሳ ሲኖረው ገርቢቾ 5 ጎሳ ኖሮት አንድ ላይ 14 ጎሳዎች ናቸው።

በአፈታሪኩ መሰረት ሹመት የሚሰጠው ከነዚህ ጎሳዎች ውስጥ ሲሆን በዚህ የአስተዳደር ስርዓት ውስጥ ለመሪዎች ሹመት የሚሰጠው በምርጫ ሳይሆን የራሳቸውን ስርዓትና ደንብ ተከትለው በባህላዊ ሹመት አሰጣጥ ስርዓት ነው። በዚሁ መሰረት በአስተዳደር ስርዓታቸው ውስጥ አራት(4) ተቧሚዎች ይገኛሉ አሉ።

1. "ጋና" በሆሎ ስር ካለው አበዶ ከሚባል ጎሳ የሚሾም ነው።
2. "ዎማ" በሆሎ ስር ካለው ሾንቶሬ ከሚባል ጎሳ የሚሾም ነው።
3. "ቃሪቻ" በሆሎ ስር ካለው ሀናፋ ከሚባል ጎሳ የሚሾም ነው።
4. "ጋደላ" በገርቢቾ ስር ካለው ገርቤ ከሚባል ጎሳ የሚሾም ነው።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1-3 የተዘረዘሩት "ሆሎ" ከሚባለው ጎሳ ስር ያሉ ሲሆኑ በተራ ቁጥር 4 የተመለከተው ደግሞ "ገርቢቾ" ከሚባለው ጎሳ ስር ያለ ነው።በዚሁ መሰረት ከሆሎ እና ከገርቢቾ ጎሳ ስር ያሉ ጎሳዎች በሲዳማ ውስጥ በየወረዳው እና በየቀበሌው የሽማግሌዎች አደረጃጀት አለ።ሁሉም መንግስታዊ አደረጃጀት ውስጥ ሳይገቡ "አፍኔ" የሚለውን በመከተል ያስተዳድራሉ።አፍኔ ማለት "ሰምታችኋል?' እሺ ተስማምተናል" እያሉ እውነቱን እየዘረዘሩ የሚነጋገሩበት ስርዓት ነው።

ስልጣኑን የያዘው ሰው ሲሞት በቦታው የሚተካው ልጅ ነው።ካሉት ወንድ ልጆች ውስጥ ያላገባው አንዱ በቦታው ይተካል።የሚተካው ልጅ የሚመረጠው በህዝብ ሳይሆን ሌላ መስፈርት አለ።መጀመሪያ ሁሉም ወንድ የሆኑ ልጆች ለቀጣዩ ተተኪነት በትጋት ልመና ሲያደርጉ ይቆያሉ።ቀኑ ደርሶ አባት ሲሞት ልመናው ይቀጥላል።በዚሁ ሁኔታ ሳለ ለአንድ ላልተገመተ ሰው ህልም አሳይቶ በህልሙ መሰረት ተጨማሪ ታላላቅ የተባሉ ሰዎች ሁኔታውን ተወያይተውበት ሹመቱ ይፀድቃል።በሹመቱ ዕለት በቦታው በርካታ ሰዎች ይገኛሉ። እንዲሁም በርካታ ስእለት ይገባል።በዚሁ ቦታ እና ዕለት ሹመቱ የፀደቀለት ልጅ አባቱ ያርድበት በነበረው ቢላዋ እንዲያርድ ይደረጋል።



ፎቶ 5 የሹመት መዋቅር



ፎቶ 6 ጋና ፍርድ የሚሰጥበት ቤት

2.4 የዳኝነት አሰጣጥ ስርአት

አራቱ ተመራጮች ወይም ስራ አስፈፃሚዎች (ጋና ፣ ዎማ ፣ ቃሪቻ ፣ ጋደላ) ለየብቻቸው የራሳቸው ክፍል፣ ዙፋን፣ ለባለጉዳዮች ማረፊያ እና ሌሎች ስርአቱን ለሚከታተሉት ማረፊያ የሚሆን ቦታ ቤት ውስጥ አላቸው። ባለጉዳዮች ሲመጡ ከአጥር በር ጀምሮ አቀባበል ተደርጎ እንደ አስፈላጊነቱ ከአራቱ በአንዱ ክፍል እንዲስተናገዱ ይደረጋል። በክፍል ውስጥ "አፍኔ" የሚለውን ስርአት በመከተል "ሰምታችኋል? እሺ ተስማምተናል" ብለው ሁኔታውን እየዘረዘሩ በመነጋገር ምርመራው ይከናወናል።

የዳኝነት ስራው ውሳኔ ቀንም ሊሊትም ይከናወናል። የዳኝነት አሰጣጡ ቀጠሮ የሚበዛበት ከሆነ ቢበዛ 45 ቀናት ሊቆይ ይችላል። የዳኝነቱ ፍርድ ሲጠናቀቅ በሁለቱም ወገን ያሉትን አስታርቀው፣ አገናኝተው፣ አስተቃቅፈው፣ አብረው አብልተውና አጠጥተው ይሸኛሉ። አሰፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሁለቱን ጎሳ አሰባስበው አወያይተው ያስታርቃሉ። በዎማ፣ ቃሪቻ ወይም ጋደላ ፍርድ የተፈረደበት ሰው በፍርዱ ቅሬታ ካለው ወደ ጋና ሄዶ ይግባኝ ይጠይቅና የመጨረሻ ውሳኔ ጋና ይሰጣል።በአፍኔ ንግግር ሠዓት ሀሰት የሚናገር ካለ ይቀሰፋል ተብሎ ይታመናል።በዚህ ቦታ ላይ በሀሰትም የሚመሰክር/የሚከራከር ካለ ከነዝርያው ያልቃሉ ተብሎ ይታመናል።የማውጣጣት ስራው ሲከናወን ጥፋቱን ያመነ ይቅርታ ይደረግለታል። እንዲሁም እዳ ካለበት ካለው ወዲያውኑ ይከፍላል። ከሌለው ደግሞ እየሰራ እንዲከፍል ይደረጋል።ከዋሸ ወይም ሌላ ጥፋት ደግሞ ካጠፋ ግን ከአካባቢው ሕብረተሰብ በማንኛውም ነገር ይገለላል። ጥፋት አጥፍቶ በፍርዱ ላይ የካደ ሰው ቢያጋጥም ከሳምንት በላይ እድሜ አይኖረውም ይሞታል ተብሎ ይታመናል።

2.5 በአቦ ወንሾ ክልል ላይ የሚገኘው ደን ሁኔታ

የአቦ ወንሾ የደን ክልል 92.34 ሄክታር ስፋት ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሁሉም ቦታ በደን የተሸፈነ ነው። ጥቂት ግቢ ውስጥ ቤት የተሰራበት ቦታ ብቻ እንጂ ቀሪው በሙሉ በተለያዩ የተፈጥሮ ዛፎች የተሸፈነ ቦታ ነው።

በዚህ የደን ክልል ውስጥ በርካታ የተፈጥሮ ዛፍ ዝርያዎች ያሉ ሲሆን ጥቂቱን ለመጥቀስ ጥቁር እንጨት ፣ አዛምር ፣ ዝግባ ፣ ጥድ ፣ ሾላ ፣ ቀርከሀ ፣ ዋንዛ ፣ ብሳና ፣ ዶቅማ (ቢተክሉት ለመብቀል የሚያስቸግር) ፣ ኮርች ፣ ቀራሮ እና ሌሎችም የዛፍ ዝርያዎች በደኑ ውስጥ ይገኛሉ። ይህ ደን በመከበሩ በርካታ እንስሳዎች እና አዕዋፎች በውስጡ የሚገኙ ሲሆን እንደሚዳቋ ፣ ጅብ ፣ ነብር ፣ ድኩላ ፣ ጦጣ ፣ ጉሬዛ እና የመሳሰሉ የዱር እንስሳት እና የተለያዩ አዕዋፎች በደኑ ውስጥ ይገኛሉ። በዚህ ደን ውስጥ ያሉ እንስሳቶች እና አዕዋፎች የቦታው ሀብት ስለሆኑ ማደን የተከለከለ ነው።









ፎቶ 7 በአቦ ወንሾ ክልል ደን ውስጥ የሚገኝ የዛፍ ዝርያ በከፊል

ይህ ደን በዚህ ልክ ተከብሮ ያለው ጠባቂ ተቀጥሮለት ወይም መንግስት ባወጣው ህግ ሳይሆን በባህላዊ ጥበቃ ስርአት ነው። በባህላቸውና በአምልኮአቸው መሰረት ከክልሉ ውስጥ ዛፍ መቁረጥ የተከለከለ ስለሆነ ማንም ሰው ምንም አይነት ዛፍ መቁረጥ አይችልም። ቦታው እየተመራ ያለው በተወከሉት የጎሳ መሪዎች ሲሆን ባህላዊ እምነቱን ባለማክበር/ህጉን ተላልፎ ከዚህ ክልል ውስጥ ዛፍ የሚቆርጥ ቢኖር ወዲያው ይቀሰፋል ተብሎ ይታመናል። ዛፎች አርጅተው በራሳቸው ካልወደቁ በስተቀር ማንም አይቆርጥም። ራሳቸው ሲወድቁ ግን በብዛት ለግቢው አገልግሎት እንዲውል ይደረጋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለግቢው አባቶች ተነግሮ ይፈቅዱና ለተቸገሩ ሰዎች ሊሰጥ ይችላል።

2.6 የአቦ ወንሾ ስርአት በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያበረከተው አስተዋጽኦ

የአቦ ወንሾ ቦታ በባህላዊ እምነት ምክንያት አካባቢው እንዳይራቆት ፣ እንዳይጎዳ ፣ እንዳይቆሽሽ እና የአየር ንብረት እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። "ግቢዬን ፣ ውሃዬን ከጠበቅህ ካፀዳህ እኔም አንተንና ቤተሰብህን እጠብቃለሁ" በሚልና በሚታይ ህልም አካባቢው እንዲጠበቅ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል።

በግረቢው ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ቤቶች የተሰሩበት ከጣራው ቆርቆሮ በስተቀር ቀሪዎቹ የተፈጥሮ ውጤቶች መሆናቸው እና በፕላስቲክ የተሰራ ነገር አለመኖሩ እንዲሁም በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች በሙሉ አካባቢን ከማቆሸሽና ከጉዳት አድኖታል።

ባህላዊ እምነቱን ባለማክበር/ህጉን ተላልፎ አካባቢውን ሊጎዳ የሚችሉ የተከለከሉ ነገሮችን አንድ ሰው ካከናወነ ይሞታል የሚል እምነት መኖሩ ደኑ ተከብሮ እና አካባቢው ፅዱ ሆኖ የአየር ንብረቱ ሳይበከል እንዲቆይ እድል ፈጥሯል ።

በባህላዊ እምነቱ የተቀመጠውን ህግ ያልተከተለ/የሻረ ሰው ቢኖር በማንኛውም ነገር ከአካባቢው ሕብረተሰብ እንዲገለል መደረጉ በተጨማሪ አካባቢው እንዳይጎዳ አድርጎታል።

በዚህ ባህላዊ እምነት ምክንያት ደኑ በመከበሩ በአካባቢው የዝናብ እጥረት አጋጥሞ እንደማያውቅ ተነግሮናል። በሌላ በኩል የመሬት መሸርሸር እንዳይከሰት ከማድረጉም በላይ በአካባቢው በረሃማነት እንዳይፈጠር ረድቷል ። እንዲሁም ብዛት ያላቸው ምንጮች እንዲፈልቁ ረድቷል ፣ የአካባቢው አየር ንብረት ለጤና ምቹ እንዲሆን አድርጓል።



ፎቶ 8 ደኑ በመከበሩ ከፈለቁት ምንጮች ውስጥ አንዱ

በአጠቃላይ አካባቢን የሚጎዳ ሕገ-ወጥ ተግባራት እንዳይከናወኑ በባህላዊ እምነቱ በኩል የተቀመጠ መመሪያ በመኖሩ ቆሻሻ እንደፈለጉ ያለአግባብ በአካባቢው አይጣልም ፣ አገልግሎት ላይ የዋለ ፕላስቲክ በየቦታው አይጣልም ፣ የደን ምንጠራ/ሕገ-ወጥ ዛፍጨፋም አይፈጸምም። ሕብረተሰቡን ከዚህ ሁሉ ክልከላ እንዲታቀብ ያደረበው መንግስት ያወጣው ህግ ሳይሆን በባህላዊ እምነቱ የተቀመጡ የአካባቢውን ሕጎችን ለማክበር በአእምሮ ውስጥ ያለው አስተሳሰብ ራሱ ስለሚያስገድደው ነው።

3 ያጋጠሙ ችግሮች

- በወረዳው በሰነድ ተመዝግቦ የተቀመጠ መረጃ አለማግኘት
- በቃል የሚሰጠንን መረጃ ተጨባጭ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ከባድ መሆኑ

